# ምዕራፍ አንድ

## ባህላዊ ልብሶቻችን

እኛ ኢትዮጵያውያን እንደየባህላችን የተለያየ ቅርጽና ቀለም ያሸበረቁ የባህል ልብሶች አሉን፡፡ እነዚህ የባህል ልብሶች የማንነታችን መገለጫዎች ናቸው፡፡ ውብ አለባበሳችን ኢትዮጵያውያንን ከሌሎች የዓለም ህዝቦች የተለየን ያደርገናል፡፡ ወደተለያዩ የውጪ ሀገራት ብንሄድ እንኳ በአሸብራቂ የበህል ልብሶቻችን አማካይነት ኢትዮጵያዊነታችንን እንገልፅለን፡፡







LIVEWORKSHEETS

እነዚህ የባህል ልብሶቻችን የራሳችንን የዕደጥበብ ፈጠራ ያሳያሉ። ለልብሶቹ የሚውለው ጥሬ እቃ የሚመረተውና ወደልብስነት የሚቀየረው በራሳችን ጥበበኞች ነው ፡፡ እነደየባህሉ እና እንደየወቅቱ የሚለበሱ ልብሶች የሃገራችንን ሽማ ሠሪዎች ችሎታ አጉልተው ያሳያሉ። በልብሶቹ ላይየሚታዩተ ጥልፎች ጌጣጌጦችና ጥበቦች ህብር ፈጥረው ቀልብ የሚስቡት በእኛው ጥበበኞች ተሰርተው ነው ፡፡ አልባሳቱ በእኛው በእኛው ስለሚቀርቡ በራሳችን ዕደጥበብ እነእድንተማመን ያደርጋሉ ፡፡



የባህል ልብሶቻችን ከጊዜ ወደጊዜ ዓለማቀፋዊ ተወዳጅነታቸው እየጨመረ መጥቷል። በየጊዜው ወደኢትዮጵያ የሚመጡት ቱሪስቶችም አለባበሳችንን እንደወደዱት በተለያዩ አጋጣሚዎች ይገልፃሉ። ባህላዊ ልብሶቻችንን ገዝተው የሚለብሱት የውጪ ዜጎች ቁጥርም ቀላል አይደለም። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ከጥጥ ስለሚዘጋጁ ምቾትና ውበት አላቸው። በማንኛዉም ጊዜ ሊለበሱ ይችላሉ። በሥራ ቦታ፣ በሰርግ፣ በበባዓላት ፣ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ወዘተ እንዲለበሱ ሆነው ስለሚዘጋጁ ተመራጭነታቸው የጎላ ነው ፡፡

ስለሆነም ኢትዮጵያውያን በእነዚህ አስደሳች የባህል ልብሶቻችን ልንኮራ ይገባል። የባህል ልብሶቻችን የኢትዮጵያዊነት መለያ እንዲኖረን ያደርጋሉ። እንደየባህሉ ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች የሚዘጋጁት የተለያዩ ልብሶች የየባህሉ አሻራ ይታይባቸዋል። ውበታቸውም ቢሆን ከውጪ ሀገራት ከሚመጡት ዘመናዊ ልብሶች የተሻለ ነው ፡፡ በጥበበኞቹ ኢትዮጵያውያን ሽማ ሰሪዎች ስለሚዘጋጁ የሀገር ውስጥ ገቢን ከፍ ያደርጋሉ። የሀገራችንንም የጥበብ ደረጃ ያሳድጋሉ። ሁላችንም ብንለብሳቸው ደግሞ አምረን ከመታየት በተጨማሪ በየጊዜው እንድናሻሽላቸው ዕድል ይፈጥራሉ። የማንነታችን መገለጫ የሆኑትን ባህላዊ ልብሶቻችንን ለቀጣዩ

ትውልድ ማስተላለፍ የምንችለውም እኛው እራሳችን ስንለብሳቸው ነው ። በባህላዊ ልብሶቻችን ተዉበን መጪው ትውልድ እንዲዋብባቸው ልናስረክብ ይገባል። << ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ፣ ባለዕዳ አይቀበለውም>> እንደሚባለው ባህላዊ ልብሶቻችንን ሌሎች እንዲቀበሏቸውና እኛ ልናከብራቸው እና ልንቀበላቸው ይገባል ።

I. ለሚከተሉት ቃላቶች ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆኑትን ምረጡ

1. ያሸበረቁ

ሀ) ያማሩ ለ) የደመቁ ሐ) የተዥጎረጎሩ መ) የተብለጨለጩ

2. የጎላ

ሀ) የተለየ ለ) ከፍያለ ሐ) የወፈረ መ) የላላ

3. አሻራ

ሀ) ምልክት ለ) መለያ ሐ) መገለጫ መ) ሁሉም

4. ህብር

ሀ) ቅልቅል ለ) ውህደት ሐ) አንድነት መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

5. ዕደጥበብ

ሀ) የጥበብ ዓይነት　　ለ) የእጅ ጥበብ　　ሐ) የጥበብ ቀሚስ　　መ) እጀ ጠባብ

6. ቀልብ

ሀ) የቀለለ　　ለ) መቅለብ　　ሐ) ኃሳብ　　መ) ቅብብል

7. አሞሌ

ሀ) ሞላላ　　ለ) ሙልሙል　　ሐ) ጨው　　መ) ኮምጣጤ

8. ሸማ

ሀ) ሻማ　　ለ) ልብስ　　ሐ) ሸብሸብ　　መ) ሻሽ

II. የሚከተሉተን ቃላት በትክክለኛ ቦታቸው በመፃፍ ዓረፍተ ነገሮችን አሟሉ፡፡ ( ትክክለና የሆነውን ቁጥር በባዶ ቦታው ላይ አስቀምጡ)

1. ቀለም　　2. ባህላዊ　　3. ቀልብ　　4. ህብር

5. ውበት　　6. ሸማ　　7. ቁጥር　　8. አሻራ

1. ባህላዊ ልብሶች የሀገራችን..................ሠሪዎች ችሎታ አጉልተው ያሳያሉ፡፡

2. ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች የሚዘጋጁት ባህላዊ ልብሶች የየባህሉ................አርፎባቸዋል፡፡

3. ብሔር ብሔረሰቦች የተለያየ............... ያላቸው የባህል ልብሶች አሏቸው፡፡

4. ባህላዊ ልብሶቻችን ከጥልፎችና ከጥበቦች ጋር.................. ፈጥረው................ ይስባሉ፡፡

5. በዐውዳመት ጊዜ ብዙዎቻችን.............. ልብስ መልበስ እንወዳለን፡፡

LIVEWORKSHEETS